ርእሰ አንቀጽ

# ክርስቶስ በእውነት ተነሥቷል

የመነሣት ዓይነቱ ብዙ ነው ፤ ወድቆ መነሣት ፤ አንቀላፍቶ መንቃት ፤ ከተቀመጡበት ብድግ ማለት ትን
ሣኤ ሲባል ፤ አግኝቶ ማጣት ፤ ተዋርዶ መክበር ፤ ተሽሮ መሾም ወዘተ የመሳሰሉትም ሁሉ የትንሣኤን ተግባር የሚ
ያመለክቱ ናቸው ።

እንዲሁም ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ያስተምርበት በነበረው ጊዜ የአራት ቀናት ሬሳ አልዓዛርን የዕ
ለት ሬሳ ወለተ ኢያኢሮስን (የኢያኢሮስን ልጅ) አሥነሥቶ ነበር፤ይሁንእንጂእነዚህክርስቶስያስነሣቸውምቢሆኑ
ሁለተኛ ሞተዋል አሁን ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ትንሣኤ በመጠባበቅ ላይ ናቸው ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ግን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሁሉ ግንኙነት የለውም
ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅሎ ሞቶ ፤ ተነሥቶ ለሰው ልጆች ሁሉ በጠ
ቅላላ የነፍስ ነፃነታቸውን እንደሚያጐናጽፋቸው ቀደም ብሎ በነቢያት ተነግሮ ነበር ።

ይህንን የተነገረውን ቃለ ትንቢት ለመፈጸም ሲል ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ተወ
ለደ ፤ ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴት የተወለደውን"
በማለት ጠቅሶ ተናግሮታል ገላትያ 4 ፡ 4 ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ከኃጢአት በስተቀር የሰው ልጆች
የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ እየሠራ ቀስ በቀስ አድጓል ፤ ለዘመዶቹ በመታዘዝ ፤ የወገኖቹን ባህልና ልማድ እያከበረ እን
ዳደገ ወንጌላዊው ሉቃስ ሲያስረዳ "ከእነርሱ ጋር ወደ ናዝሬት መጣ ፤ ለእነርሱም ይታዘዝ ነበር ። ኢየሱስም በጥ
በብና በቁመት ያድግ ነበር በጸጋም በእግዚአብሔር በሰውም ዘንድ" ይላል ሉቃስ 2 ፡ 40 ። 51 - 52 ።

ይሁን እንጂ ክርስቶስ ወደዓለም የመጣው በትዕዛዝ መተላለፍ የተነጠቀውን የሰው ልጆች ክብር መልሶ
ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማጐናጸፍ ስለሆነ ይህንን ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ከማከናወን
ወደኋላ ያለበት ጊዜ የለም ። የሰው ልጅ ደኅንነት ሊሰጥ የሚችለው በራሱ መሥዋዕትነት መሆኑን አስቀድሞ ያውቀ
ዋልና ልዩ ልዩ መከራን ከተቀበለ በኋላ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለይቷል የዮሐንስ ወንጌል
19 ፡ 30 ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎ ፤ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በመነሣት
ዓለምን ከፍዳና ከመርገም እንደሚያድን ቀደም ብሎ የተነገረ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች የተነገረውን ትንቢት አላመ
ኑም ነበር ፤ ካለማመናቸውም የተነሣ በክርስቶስ ላይ የሞት ፍርድ ፈርደው ፤ ሰቅለው ከገደሉት በኋላ ሥጋው ወደ
መቃብር ከወረደ ጀምሮ መቃብሩን በፈረቃ የሚጠብቁ ጭፍሮችን መድበው መቃብሩን ነቅተው እንዲጠብቁ
አድርገው ነበር ፤ ቢሆንም ጌታችን ክርስቶስ መቃብር ክፈቱልኝ ፤ መግነዝ ፍቱልኝ ፤ ደንጊያ ፈንቅሉልኝ ሳይል
በዚያው በተሰፋው መሠረት በሦስተኛው ቀን ተነሣ ፤ በተነሣም ጊዜ መቃብሩን ነቅተው እንዲጠብቁ በፈረቃ
የተመደቡት ዘበኞች እየሰሙ እንደማይሰሙ ፤ እያዩ እንደማያዩ ሆኑ ።

በዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ክቡር ዳዊት "እግዚአብሔር ይነሣል ፤ ጠላቶቹም ይበተናሉ ፤ እግዚአብሔርም ከእ
ንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ" በማለት የተናገረው ቃለ ትንቢት ፍጻሜውን አገኘ (መዝ.67 ፡ 1 ፤ 77 ፤ 65 እንዲሁም
ሐዋርያው ጳውሎስ "ሞት በመሸነፍ ባሕር ተዋጠ ፤ ሞት ሆይ ! መውጊያህ የት አለ ? ሲኦል ሆይ ! ማሸነፍህስ የት
ነው"? ብሎ እንደተናገረው በክርስቶስ ትንሣኤ የሞት ኃይሉ ደከመ ፤ ሥልጣኑም ተሻረ ፤ ተደመሰሰ ፤ ክርስቶስ
ንም ይዞ ለማስቀረት አልቻለም 1ኛ ቆሮ 15 ፡ 54 ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ከርሠ መቃብር በወረደ በማግሥቱ እነ ማርያም መግደላዊት ሽቱን አዘጋጅ
ተው የክርስቶስን አካል ለመቀባት ወደመቃብሩ ተጉዘዋል ፤ ከመቃብሩ እንደደረሱ ግን የክርስቶስን መቃብር እንደ
ሚገባ ሆኖ አላገኙትም ፤ መቃብሩ ተከፍቶ በመቃብሩ ላይ የነበረው ደንጊያ ተፈንቅሎ ፤ በተፈነቀለው ደንጊያ ላይ
ም ፤ አንድ ነጭ ልብስ የለበሰ መልአክ በማየታቸው በፍርሃትና በድንጋጤ ተዋጡ ፤

መልአኩም መፍራታቸውንና መደንገጣቸውን አውቆ አይዟችሁ ! አትፍሩ ! አትደንግጡ ! የተሰቀለውን
ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና ክርስቶስ አሁን ከዚህ የለም ተነሥቷል ፤ በማለት መልአኩ የክርስቶስን መነ
ሣት በመጀመሪያ ለቅዱሳት አንስት አብሥሯቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

መልአኩ ይህንን መልካም ወሬ (የምሥራች) ለቅዱሳት አንስት ያበሠራቸው በምሥጢር ጠብቀው እንዲ ይዙት ሳይሆን ባስቸኳይ ሂደው ለደቀ መዛሙርቱ እንዲናገሩ ጨምሮ አዝዟቸዋል ፤ እነርሱም እንደታዘዙት ሂደው የክርስቶስን መነሣት ለሐዋርያት ለማብሠር ችለዋል ።

ክርስቶስ ስለእኛ በደልና ኃጢአት ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ከፍዳና ከመርገም ነፃ አድርጐናል ከእንግዲህ ወዲህ ግን እኛ ከሕግ ወጥተን ብንበድል ክርስቶስ ሁለተኛ ስለእኛ ኃጢአትና በደል አይሞትልንም ፤ በዕርግጥ ክር ስቶስ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም ይመጣል ፤ ግን የሚመጣው ስለ ኃጢአታችን ሁለተኛ ለመሞት ሳይሆን አዝክሮተ ፍቅር ለጻድቃን አዘክሮተ በቀል ለኃጥአን ለማድረግ ነው ።

እኛ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን መጠን ስለ ክርስቶስ መከራና ሥቃይ መሞትና መነሣት እንዲሁም ስላደረገልን ቸርነት የመመስከር ግዴታ አለብን ለምንሰጠውም ምስክርነት ልዩ ልዩ ምክንያ ት መስጠት አይገባንም ሐዋርያው ጳውሎስ "ለነፃነታችሁ ምክንያት አትስጡ" ይላል ክርስቶስ ብዙ ፀዋትወ መከ ራን ተቀብሎ ሞቶ ተነሥቶ በትንሣኤው ያጐናጸፈንን ነፃነት በማይገባ ምክንያት ከእኛ እንዲነጠቅ ማድረግ አይገ ባንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን ነፃነት ለሁልጊዜ ከእኛ ጋር እንዲኖር ክርስቶስ በእውነት ተነሥ ቷል እያልን መናገር ፤ መመስከር ፤ ማስተማር ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው ፤ ለዚህም መንፈሳዊ ተግባር ወንድ ሴት ትንሽ ትልቅ አያሰኝምና ሁላችንም በኅብረት "ክርስቶስ ተነሥቷል" የሚለውን የምሥራች ቃል ላልሰሙት እናሰማ ።

ትንሣኤ ቁጥር 19 ሚያዝያ 1971